# የዲያስፓራ ባንዳ ምሁራንና ባንዳ ደናቁርት አገር ላይ ዱለታ

ከታጠቅ ጀግናው

የድሮዎቹ ባንዳዎችና የዘመኑ ባንዳዎች አገርና ሕዝብን ለውጭ ጠላት አሳልፎ የመሸጥ ተግባራቸው አንድ ያደርጋቸዋል፡፡ ልዩነታቸው የዘንድሮቹ ምሁራንና ዶክተር ዜሮዎችን ማፍራቱ ነው። ዛሬ በባንዳ ምሁራን ሳንባ የሚተነፍሱት ባንዳ ደናቁርት የፓለቱካው ሀሁ ስለማይገባቸው አገርን እያፈረሱ ወደ መቀመቅ ሲነግዱ ላያቸው መሳቂያ ሆነዋል፡፡ የባንዳዎቹ ኢትዮጵያዊ ፍቅር የተንሸዋረረ ማለትም ኢትዮጵያን የሚያዩ መስለው በተግባር የሚየዩት ግን ሻቢያን ነው፡፡ ለማረጋገጥ ዲያስፓራው ውስጥ ርቃችሁ ሳትሄዱ በምትኖሩበት ቁ በግላጭ አሉላችሁ፡፡ ምናልባት ባካባቢያችሁ ባንዳ ምሁራን ባታዪ አትደነቁ፡፡ ከሌላ ቀረብ ካለ ስቴት በመሆን ለባንዳ ደናቁርቱ መመሪያ በቴሌፎን፡ በቴሌ ኮንፍረንስና በፓልቶክ ይሰጧችዋል። ኢትዮጵያውያን በምንኖርበት ሁሉ ባንዳ ደናቁርቱ የሚያስደነግጥ ቁጥር ባይኖራቸውም አገርንና ሕዝብን ለማድማትና ለማዋረድ ሌት ተቀን ሲሯሯጡ ማየቱ ግን ያሳዝናል።

የዲያስፓራው ባንዳ ከሻቢያ ይወለዳል፡፡ የፓለቲካ ጉዟቸው አግር ማፍታታቸው የሚጀምረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃቀኛ ልጅ የሆነውን ኢሕ አፓን በመኮነን፣ በመሳደብና በማጥላላት ነው፡፡ ወያኔን ከሚጠሉና ከሚታገሉ ይልቅ የትግል ፍጆታ ማገዶአችውን የሚጨርሱት በኢሕ አፓ ላይ ነው። ቀጥሎም ትግሉን ድንቁም የትጥቅ ትግሉን ለመጀመር ቦታ የሚገኘው ኤርትራ ነው ብለው ለሰሚ የማይጥም ቱልቱላ መንፋት ይጀምራሉ፡፡ ከኢሳያስ በላይ ዲሞክራሲን የሚያራምድና ሰብዓዊ መብትን የሚያስከብር መሪ አልተወለደም፡፡ ወደፊትም አይወለድም ያስብላሉ በምርጥ ባንዳ ምሁራቸውና እንደ አበደ ውሻ በሚያክለፈልፋቸው ባንዳ ደናቁርት ወታደሮቻቸው። እንኳን ከሻቢያ ወያኔን ለመጣል ከሰይጣንም ጋር እንሰራለን ይሉናል፡፡ ያልገባቸው ሕዝብ ሰይጣንን እንደማይፈልግ ነው፡፡ ከሰይጣን ጋር የሚሰራ ሰይጣን እንጂ ሰው አይደለም፡፡ ወያኔ እኮ ለስልጣን የበቃው የሱዳንን መሬት ተጠቅሞ ነው የሚል ሌላ አፍዝ አደንግዝ ሊነፉብንም ሞክረዋል፡፡ ወያኔ ሱዳን እንደነበር ማን ይክዳል፡፡ ያ አይደለም ቁም ነገሩ፡፡ ወያኔ ለስልጣን የበቃው፡

1. ደርግ ጸረ-ሕዝብ በመሆን ሕዝቡን ወኔ ቢስ በማድረጉ
2. ወያኔ ይህ ነው የማይባል ዕርዳታና ድጋፍ ከአገር አጥፊው ሻቢያ በማግኘቱ
3. የኢትዮጵያን ሉዓላይነና የሕዝቧንም አንድነት በማይወዱ ሃያላን መንግስታት ድጋፍ
4. በደርግ ውስጥ ተሸጉጠው መረጃ በሚያቀብሉ ባንዳዎች በተለይም ባንዳ ምሁራን
5. ኢትዮጵያዊ የሆነው የተቃዋሚ ጎራ ባለማበሩ

ከደርግ ምን የማይሻል አለ የሚለው አባባል የደርግን ፋሺስታዊ ገጽታ በቅጡ የሚገልጽ ቢሆንም እየመጣ ያለውን የወያኔና የሻቢያን ምንንነት በሚገባ አለመረዳቱም በላያችን ላይ ያመጣነው ጸጸት ሆኖብናል፡፡ ደርግ አገርን ከመከላከል ተፈጥሮው በመውጣት የማያውቅበትን የፓለቲካ አመራር ጨብጦ ለሌላ አገር አጥፊ ጠላት አጋልጦን ፈረጠጠ። ያለጠባቂ እርቃኗን የቀረችውን ኢትዮጵያ የወያኔና የሻቢያ ጀሌዎች ተንሰራፉባት፡፡ ባዶ ኪስ የገባው ዘረኛ፣ አምባገነንና አገር ገዳይ የሆኑት ወያኔና ሻቢያ ያለገላጋይ የአገሪቷን ሃብት ዘረፉ፡፡ ባንድ አጭር ምሽት ከበርቴዎች ሆኑ። ሲሰርቁ የተሰማሙት ወያኔና ሻቢያ ሲከፋፈሉ ባለመስማማታቸው ተጣሉ፡፡ የኢትዮጵያ ሁለት ጠላቶች መንገዳቸውን ለየቅል ቢያደርጉም አንዳቸውም ኢትዮጵያን ከማሽመደመድ አላባሩም።

ወያኔ የኢትዮጵያዊያንን ወኔ በዘር ለማኮላሸት የሚያደርገው ሴራ በባንዳዎችና እበላባዮች ቢከቸለቸልም የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ ግን መግዛት አልቻለም። ሻቢያም ኢትዮጵያን ለማሽመድመድ በዘር የተደራጁ ቡድኖችን ማበርከቱን አልተወውም። የዚህ ጎሳ ነን ባይሉም ግን ኢትዮጵያ የሚለውን ሃያል ቃል የማያንጸባርቁ አዲስ የፓለቲካ ድርጅት ጉዶችን ግን ማጎልበቱን ተያይዞታል። ኢትዮጵያ የሚል ስም ካላነሱለት ሻቢያ ሰኔ መስከረም ብጫ . . . ብሎ ለኢትዮጵያ የማይበጅ ግርግር ቡድን መፍጠሩን ይወደዋል፡፡ አንድ መስመርም ይሆን አንድ ሺህ መጽሃፍትም ተጻፈ ወያኔም ኖነ ሻቢያ መሰረታዊ የኢትዮጵያ ጠላቶች ናቸው፡፡ ይህን ሃቅ የማይቀበል ወይ ባንዳ ምሁራን ናቸው አለያም ባንዳ ደናቁርት ናቸው።

ጊዜ መስታውቱ ገና ብዙ ልናይበት አይደል? ሻቢያ የኢትዮጵያ ጠላት ሆኖ አያውቅም ሲባል መስማት ከጀመርን ቆየን። ወያኔን ለማጥፋት ከሰይጣንም ጋር ቢሆን እንተባበራለን ያለን ሰይጣን ሻቢያ ሰይጣን ወገኑ ስለመሆን አለመረዳቱ ይገርም ኢትዮጵያ ማለት አስገደደን። ስልቻ ቀልቀሎ ወያኔ ሻቢያ ምን ለያቸው? አንድ ወገኔ ሻቢያ ለባንዳ ምሁራን የረፍት ቦታ

በማዘጋጀት ኣቢያን የሚያፈቅሩ ኢትዮጵያውያንን በከረን በአስመራና በምጽዋ እያዝናና ነው ያለኝን ሳስበው ይገርመኛል። ዕውነቱን እኮ ነው። ኤርትራ የግንቦቴዎችና የዘረኛ ቡድኖች የመዝናኛ መንደር ሆነች ሰማሁና ወይ ዲያስፓራ ብራችሁ የት እንደሚሄድ ሰምታችሁ ይሆን ብዬ ለመጠየቅ ፈለግሁ፡፡ አንዱ ጓደኛዬ ደግሞ ዲያስፓራው እኮ ሞኝ ነው፡፡ እናትህን የማርድበት የሳለ ቢላዋ መግዣ ቢላዋ አጣሁ ቡሉት ኪሱን ዘቅዝቆ ገንዘቡ ሁሉ ይሰጣ ቢለኝ ዘገነነኝ። ግን ዕውነት ሆነና አዘንኩ።

ወያኔ ዘረኛ ነው። ወያኔ በዝባዥ ነው። ወያኔ አምባገነን ነው። ወያኔ ገዳይ ነው። ወያኔ በዲሞክራሲ የማያምንና ሰብዓዊ ሙብትንም የማይከብር ነው። ለመሆኑ ለሻቢያ ለወያኔ ከሰጠሁት ውስጥ የሚያንሰው ወይም የሚበዛበት ነገር ይኖር ይሆን? ለኔ ወያኔም ሻቢያም ከላይ ያልኩትን እኩል ይጋራሩ። ለሁላችን መቅረብ ያለበት ጥያቄ አውን ለኢትዮጵያ ሻቢያ ከወያኔ ይሻላልን? ለኔ ሁለቱም ሰይጣን ናቸው በተራ ቃል ስገልጻቸው። ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን የሚለው አባባል ይገባኝም ነበር። አንድ ቀን ዝንጀሮዎች የሚገኙበት ቦታ ሄጄ ማወዳደ ጀመርኩ። ሁሉም ዝንጀሮ አንድ ሆኑብኝ። ቆንጆ የላቸውም። ሁሉም አንድ ዓይነት አስቀያሚ ዝንጀሮዎች ናቸው። በሻቢያና በወያኔ መካከል ልዩነት የለም። ሁለቱም አምባገነንና ኢሰብዓዊ ፍጡር ናቸው። ከሻቢያና ወያኔ ምን ይመራርጡ ትክክለኛ አባባል ነው፡፡ አዲስ ነገር ቢኖር በሻቢያና ወያኔ ጎራ ውስጥ ግንቦት ሰባት መግባቱ ነው። መግባቱ ብቻ ሳይሆን ባንዳ ምሁራኑንና ባንዳ ደናቁርቱን በማሰማራት ቱልቱላውን መንፋቱ ነው።

ዛሬ ከምድረ ኤርትራ በሻቢያ ኢሰበዓዊ አምባገነን አገዛዝ የተማረሩ 5,000 ወጣቶች በየወሩ አገር ጥለው ይሰደዳሉ። ዛሬ ኤርትራ ባዳው ለሆነው ግንቦት ሰባት የመዝናኛ መነሃሪያ ስትሆን ለዜጎቿ ሲኦል ሆናለች። የሚሰደደው ዜጋ በበረሃና በባሕር ሕይወቱ በመቀሰፍ ላይ ነው። ለግንቦት ሰባት የወያኔ ኢዲሞክራሲነትና ጸረ ሰብአዊ ምብትነት ፍንትው ብሎ ሲታየው የሻቢያው ግን ተጋርዶበታል። ለግንቦት ሰባት የኤርትራ ሕዝብ ስቃይ ቁምነገሩም አይደለም። ጉድ እኮ ነው። አንድ ድሕረገጽ ላይ ዶክተር ብርሃኑ አሕያ ተሸክሞ አየሁት። አህያን ያህል ከባድ ኢጋሰ የተሸከመው ዶክተር ምን ነካውና ነው ኢጋሰስ ያውም አሕያንድ መሸከም የፈለገው? ምናልባት አህያው ታሞ ይሆን? ታዲያ ዶክተሩ ለታመመ አህያ ያን ያህል ሰቦኣዊነትን (አህያነትን) ካሳየ ምነው በየውቅያኖሱ ለአሳነባሪ የሚዳረጉትን ፍትህ ፈላጊ የኤርትራ ወጣቶች ልቡ ጨከነ? መልሱን ባውቀውም ጥያቄውን ማቅረቡ ደግሞ ተገቢ ስለሆነ ነው።

እንዲህ ብዬ ልደምደም። ግንቦት ሰባት በባንዳ ምሁራኑና በባንዳ ደናቁርቱ ( እግረኛ ወታደሮቹ) ለስልጣን አይበቃም። ግንቦት ሰባት ለስልጣን የሚበቃው ምላኔ ጸጉር ያበቀለ ለታ ብቻ ይሆናል። ለነገሩ ግንቦት ሰባት ለስልጣንም አይበቃም ምላሴም ጸጉርም አያበቅልም። ወይም ሻቢያም ሆነ ወያኔ ኢትዮጵያን አይገድሉም ዕድሜ ለጀግና ሕዝቦቿ። ግን ይብላኝ ለግንቦት ሰባት ባንዳ ምሁራንና ባንዳ ደናቁርት። ኢትዮጵያ በሃቀኛ ልጆቿዋ ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።